# ይድረስ ለጋሼ ጸጋዬ ገ/መድኅን

**ትፍስኅተ ገነት**

**<u>መንግሥተ ሰማይ</u>**

**ቅጽ [illegible]**

**-በሴም ኩሽ (ኖርዌይ)**

**ይኼውልህ ጋሽዬ... ተተለየኸን ቀን ጀምሮ**
**ምን ያልሆነው አለ ብለህ፣ በቤታችን ዘንድሮ፤**
**"ከሞከርነው ነገር ያልሞከርነው ነው የሚቆጨኝ"**
**መይሳው ያለው ትዝ ቢለኝ፣ እግረ ኅሊናዬን ቢያድጠኝ**
**ይቺን ጦማር ላቀብልህ፣ ጋሽዬ አደራህ ጠራኝ፤**

**የዘንድሮን ጉድ ላዋይህ፣ መቼም መላ አንተ አታጣ**
**የቃሊቲው አዳል ሞቲ፣ ቦረንትቻው አጋ መታ**
**የምሱን ቢገብሩም፣ ጠገብኩ አላለም ባንዴ አያናው**
**ደም በደም ሸተተኝ ብሎ፣ ኅምቱ ኅምቱውን ጭዳ አረገው፤**
**ይኼውልህ ጋሽዬ... የበደል በደል ፍጻሜ፣ በጀግኖችህ ላይ ዋለ**
**አሞሪትን ጅግራ ብለው ሲቀረጥፏ፣ ዓለም እያየ ዝም አለ፤**
**ይኼውልህ ጋሽዬ... ከሆነው ሁሉ ያልሆነው ሞልቶ ፈሰሰ**
**"ወንጀል እንደኒሻን..." ሲታደለን፣ አገር ምድሩ ጨሰ፤**
**የሰላም እጅ ዘርግተን፣ የባንዳ አኮርባጅ ተቀበለን**
**ቀምበጥ አበባ ሰጥተን፣ ያጋዚ ጥይት ቀለበን፤**
**ይኼውልህ ጋሽዬ... በፍትኅ እጦት፣ እንዳሞሪት ስንበላ**
**ፍቅር ዘርተን፣ የዘረኝነት አረም ሁዳዳችንን ሲሞላ፤**

**ይኼውልህ ጋሽዬ... ተተለየኸን እለት ጀምሮ**
**ምን ያልሆነው አለ ብለህ፣ በመንደራችን ዘንድሮ፤**
**ያም ጋጋኖ፣ እራሱን አርጎ " ዜሮ ዜሮ..."**
**ከጌቶቹ ጋር ተሸርቶ፣ ከህዝብ ዓይን ተሸርጦ**
**ላንዲት አፍታ እሸገር ላይ ትንፋሽ አጥቶ**
**እንደሌባ ተሾልኮ እንደ ውሻ በሮ ወጥቶ**
**ተዋሽንጌቶው ጭንቡል አለ፣ ውቃቢ አምላክ ርቆት**
**"ያዝማሪ ቀልባጣ ይገባዋል..." ምናምን ብሎት**
**የጉድ አገር ገንፎው፣ እያደር ሲፋጅ አየና እንዲህ**
**ስንቱን ላውጋህ ጋሽዬ፣ ለካስ ለዚህ ነው አረህ ተክነህ መሄድህ?**

**ይሄውልህ ጋሽዬ... "ወይ ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ" ያልካቸው**
**የድረሱላት ጥሪ ስታሰማ፣ ባባትነትህ ያነጽካቸው**
**እኒያ የምዬ ልጆች ሁለት ፍሬ የናት ጡቶች ያልናቸው**
**ዛሬም ምክርክን ይሻሉ፣ ቁጣ ብእርክን ላክባቸው**
**ከሞከርነው ያልሞከርነው እንዲቆጨን፣ ባባ ታጠቅ ቃል ያዝልኝ**
**ልጅ እንዳባቱ ታልሆነ፣ እንግዲያማ ልጅነቱ በምን ለየ በልልኝ**
**እንደ እንቆቆ ቢመርም፣ ዶሮማታ ነውና ባንድ ኅራ አስገባልኝ**
**ድር ቢያብር እያልክ፣ በምኒሊክ ስም ጠፍርልኝ**

በዮሃንስ የምነት ክር፣ እስተወዲያኛው አቀይልኝ
ለዚያ ምስኪን ሕዝብ ተናንተ ሌላ...ማን አለ? በልልኝ፤

ባድሜም ድሜ አብልታን ለራሰዋም ድሜ በልታ
ድሜ በልተው ድሜ ላሰበሉን እጅ ነስታ
ይሄውና ጋሽዬ... ”ደሃን ሁኑ” አለችና
ሰባ ሺዎች እንዳልቀሩ፣ ተደጅዋና ባሊቴና
ታክስቷ ቤት ወጥታ፣ ታጎቷ ቤት ብትገባ
”አክሱም ለጋሞው ምኑ ነው?” በሚል ባንዳዊ ዘረባ
እሷ ምንተዳዋ ሽርሽሩን ለምዳው ተሹምባሹ ታጎምባሹ
የእዝን ንፍሮ ቃመዪ፣ ወገንህ ሁላ መረብ ምላሹ፤

ይሄውልህ ጋሽዬ... ተተለየኽን እለት ጀምሮ
ምን ያልሆነው አለ ብለህ፣ አገር በርሃብ ነፍሮ፣
ወገን በበሽታ ተቀይዶ፣ ባንዳ በዘኬ ቁንጣን ተንሮ
ተሆነው ይልቅ ያልሆነው ጠፋ ዘንድሮ፤
ሕንጻ በሕንጻ ሆንን፣ ሽረሪት ተድር ሊዳራበት
ነዋሪ ሰንባች ጠፍቶ፣ አንድ ሰው ብቻ ሊያልፍለት
አዳራሽ ተልፍኝ ታቅፎ፣ ባዶ አንጀቱን ሊያጥፍበት
ወግ አልቀር ብሎ፣ ዘቡሌም አለፈለት ተባለለት፤

የኔ ነገር ጋሽዬ... መንገድ ተሠራን ሳልነግርህ
በሽታና ረሃብ ላጨደው ያስከሬን መውጫ አሰበው
ችግርህ ለቀባሪው መንገድ ማግኘት ነው ብለው
ፋንፋር ጡሩምባ እያስነፉ፣ ለእድርተኛው ለፈፋለት
ሬዲዮን ከቲቪ ጋር ይጋተው ብለው ሸሙለት
ማደንዘዣ መሆኑ ነው፣ ለራብ ጥማቱ ያገር ሕመም፤

ይሄውልህ ጋሽዬ... ዘመኑ ዘመነ ግልምቢጥ ሆነ
አህያው ወደ ቤት ሲሮጥ፣ ውሻው ወደ ግጦሽ በረረ፤
የትናንት ካድሬው የልፍኝ አሽከሩ ሁላ
ላዲሶቹ ጌቶቹ እጅ ነሳ፣ ጅራቱን እንደቦቢ እየቆላ
የሌባ ዓይነ ደረቅ፣ እሱው ከሳሽ እሱው ምስክር ሁኖ
እሱው ጠቋሚ እሱው ዳኛ እሱው አቃቤ ሁኖ
የራሱን ሥራ የራሱን ግብር፣ ላቤት ባዩ አውርሶ
ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል፣ እትፋቱ ላይ አጎንብሶ፤
ይሄውልህ ጋሽዬ... አይሰሙት ጉድ የለ፣ አያስተውሉት ደባ
የሶላቶው አሽከር ልጅ፣ ያባቱን አርማ አንስቶ፣ ከጠላት ጎራ ገባ፤

እስቲ ይሁና ጋሽዬ... ሆድ እንደሁ ካገር ይሰፋል
የሞተው ነቅቶ የነቃው ሙቶ፣ ቤት እንዲህ ሁኖ ይፈርሳል፤
ታውቃት የለም?... ያቺን ጎረቤት በቤቷ ሰላም የሌላት
ልጆቿን ተዱር በትና፣ ሁለት አሠርት የቆዘመች?
የሆነችው አልበቃት ብሎ፣ በንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
በታንክ አዳፍኔ አርሷት፣ ባንድ መዓልት ሺውን ቢያረግፍ
ጋሽዬ አፈርንልህ... እንገባበት አጣን ያገር ልጆች
የናት አገር ስም ተብጠልጥሎ፣ ወራሪ ነች ተስተባለች
ሉሲፈር የፈጣሪውን ግብር በፈጸመ፣ ምሥራቅ አፍሪካን ባወከ

ነገረኛዋ ጎረቤት የጎሪጥ ታየን ብትጀምር፣ ልጇም ጠሩን ሰበቀ፤
ይሄውልህ ጋሽዬ... ነገን ለበቀል ጽዋ አፈላማ አሲዘን
ፍርሃትን በቤታችን ላይ አንግሠን፣ ሌላ ጠርነት ሌላ እልቂትን እንጠብቃለን፤

ይሄውልህ ጋሽዬ... ደሞ ዘንድሮ አዲስ ጨዋታ መጥቶ
መስከረሙ ሳይጠባ የሚሊኒዬሙ ቧልት ደርቶ-
አንዱ ጎምቱ የዘመንተኞቹ አባወራ
የቁም ኑዛዜውን በቁም ተዝካሩ ላይ ሲያዘራ-
"የሞትን ሞት አፈር እየቃምን የሞትነው፣ ለእምዬዩቱ ኤርትራ እንጂ
መች ኢትዮጵያ ለምትሏት" እያለ ቢጠቅስ አሰረጂ
ሕጣን ታዋቂ ቤቱን ዘግቶ፣ አንገቱን ደፍቶ አነባ
ኧረ ሰንቱን አየን ጋሽዬ፣ መስከረሙ ሳይጠባ፤
መታደል እንጂ ነው ጋሽዬ... ይሄን ጉድ ሳታይ መሄድህ
መቶ ዓመት ባንደዜ አድጎ፣ ይሄውልህ ተሺ ዓመት ተዶልንልህ፤
በሚሊኒዬም የጉዞ ፍታት፣ የታሪክ አስከሬን ሸኘንልህ
እኛን ያበረታ አምላክ፣ እስቲ ላንተም ብርታት ጽናቱን ይስጥህ፤

ይኼውልህ ጋሽዬ... ተተለየኸን ቀን ጀምሮ
ምን ያልሆነው አለ ብለህ፣ በቤታችን ዘንድሮ፤
"ከሞከርነው ነገር ያልሞከርነው ነው የሚቆጨኝ"
መይሳው ያለው ትዝ ቢለኝ፣ እግረ ጎሊናዬን ቢያድጠኝ
ይቺን ጠማር ላቀብልህ፣ ጋሽዬ አደራህ ጠራኝ፤

(ሰኔ 17 ቀን 1999)